# School Health Services Program
## AUTHORIZATION FOR SPECIFIC MEDICAL PROCEDURE/TREATMENT

ውድ ወላጅ/አሳዳጊ/ኃላፊ ሰው እና ሀኪም፤

በትምህርት ወቅት የህክምና ምርመራ እና/ወይንም ህክምና የሚያስፈልጋቸው ተማሪዎች የሚከተሉትን ቅድመ ሁኔታዎች ማሟላት አለባቸው።

1. ወላጆች/አሳዳጊዎች/ኃላፊ የሆኑ ሰዎች፣ ለልጆች የትምህርት ቤት አገልግሎቶች ኃላፊ (CSS) ለሆነው ባለሙያ ተጠናቆ የተሞላ እና የተፈረመበት የመድኃኒት አሰጣጥ/የህክምና አሰጣጥ እቅድ እና ወላጅ/አሳዳጊ/ኃላፊ ሰው የፈረመበት የስምምነት ክፍል I (part 1) እና የምስክር ወረቀት ያለው የጤና ሰጪ ድርጅቱ የጤና ባለሙያ፣ ለምርመራው/ለህክምናው ክፍል 2 (part 2) ፈቃድ የሰጠበት የተፈረመበት ማስረጃ ሊኖር ይገባል። የምስክር ወረቀት ያለው የጤና ጠባቂው ባለሙያ እና የወላጅ የተፈረመበት የስምምነት ቅጽ በተማሪው የጤንነት ማስረጃ ውስጥ መቀመጥ ይኖርበታል።

2. በትምህርት ቤት ለሚሰጥ ለእያንዳንዱ የምርመራ ወይንም የህክምና እቅድ፣ የተለየ ምርመራ ወይንም የህክምና እቅድ እንዲቀርብ ይደርጋል።

3. የምስክር ወረቀት ያለው ጤና ጠባቂ ባለሙያ የፈረመበት እና ህክምና እንዲደረግ ፈቃድ የተሰጠበት ወረቀት የሚከተሉትን ማካተት አለበት፤
   - የማሪውን ስም እና የትውልድ ዘመኑን፣
   - ምርመራውን፣ ምርመራ/ህክምና እንዲደረግ የተፈለገበት ምክንያት፣
   - የምርመራው/የህክምናው መጠሪያ ስም፣
   - ምርመራው/ህክምናው የሚካሄድበት ሰዓት እና/ወይንም በትምህርት ቤት ተደጋግሞ ለምን ያህል ጊዜ እንደሚደረግ፣
   - ህክምናው ለምን ያህል ጊዜ እንደሚቆይ፣
   - መደረግ ስለሚገባቸው ልዩ ወይንም የአስቸኳይ ጊዜ ህክምናዎች፤

4. ስለሚደረጉ ምርመራዎች/ህክምናዎች የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶች በውላጅ/አሳዳጊ/ኃላፊ ሰው (በተማሪው ወይንም 18 ዓመት በሞላው ወይንም ከዚህ በላይ እድሜ ባለው) መቅረብ አለበት። ለህክምና የሚያሰፈልገው ማንኛውም የህክምና መሣሪያዎች ወይንም ቁሳቁሶች የሚቻል ከሆነ በትምህርት ቤት መቀመጥ አለባችው።

5. የተሰጠባቸው የምስክር ወረቀት ባለው የጤና አገልግሎት ጠባቂ በለሙያ ሥልጣን መስጫ ወረቀቶች፣ በጤና ጠባበቃ አገልግሎት ሰጭው ባለሙያ ሥልጣን መስጫ ወረቀቶች፣ በጤና ጠባቂው ድርጅት የተፈረመባቸው ማስረጃዎች ለ 1 ዓመት ጌዜ ብቻ ነው የሚያገለግሉ።

6. ለምርመራው/ለህክምናው እቅድ አዲስ የመድኃኒት የአሰጣጥ የህክምና እቅድ የሚያስፈልገው ሆኖ ከተገኘ ማንኛውም ዐይነት አሠራር  (ለምሳሌ የህክምና ዘዴ፣ የሚሰጥበት ጊዜ ድግግሞሽ ያስፈልገው እንደሆነ።

7. በትምህርት ቤት የተቀመጡ መሣሪያዎች እና መድኃኒቶች፣ መድኃኒቶቹን በሚሰጠው ወይንም ህክምናውን በሚደያርገው ባለሙያ ብቻ ሊገኙ በሚችሉ ቦታዎች እንዲቀመጡ ይደረጋሉ። በትምህርት ቤቶች ለልጅ የሚሰጡ አገልግሎቶች (CSS) ኃላፊ ሰው እና የዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ የሕዝብ እና የሕዝብ ቻርተር ትምህርት ቤት ሠራተኛ ለሚጠፉ ወይንም ለሚበላሹ መሣሪያዎች እና የህክምና መድኃኒቶች ኃላፊነት አይወስድም።.

8. የምስክር ወረቀት ያለው የጤና ጠባቂው ባለሙያ ወይንም የመሣሪያዎቹ እና የመድኃኒቶቹ  የጊዜ ፈቃድ ካበቃ 1 ሣምንት ጊዜ ውስጥ፣ ወላጅ/አሳዳጊ/ኃላፊ ሰው፣ መሣሪያዎቹን እና ተማሪው ያልተጠቀመባቸውን መድኃኒቶች ሰብስቦ መውሰድ አለበት። ጊዜያቸው ያለፈባቸው እና በዚያን ወቅት በወላጅ/አሳዳጊ/ኃላፊ ሰው ሳይወሰዱ የቀሩ የህክምና ቁሳቁሶች እና መድኃኒቶች እንዲወገዱ ይደርጋል።

9. ለተማሪው ከደንብ ውጪ ለሚደረጉ የጤና አጠባበቅ አሠራሮች/ህክምናዎች ወይንም በራሱ በተማሪው ለሚደረጉ ህክምናዎች የ CSS ባለሙያ እና የትምህርት ቤት ባለሙያ ሠራተኞች ኃላፊነት የለባቸውም።